# የቀድሞው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠ/ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ሕልፈተ ሕይወት 1ኛ ዓመት የመታሰቢያ ሥነ-ሥርዓት በሮም



የቀድሞው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠ/ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ሕልፈተ ሕይወት 1ኛ ዓመት የመታሰቢያ ሥነ-ሥርዓት ነሐሴ 12 ቀን 2005 ዓ.ም. «ቃልህ ይጠበቃል፤ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስም ቃላችንን እናድሳለን» በሚል መሪ ቃል በጣሊያን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ተከናውኗል።

በዚሁ የመታሰቢያ መርሃ-ግብር የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት ከተደረገ በኋላ በጣሊያን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ክቡር አቶ ሙሉጌታ አለምሰገድ በወቅቱ ለተገኙት በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምሮ በኢትዮጵያ ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ እንዲሰፍንና የሕዝቦች እኩልነት እንዲረጋገጥ የታገሉና ያታገሉ ጀግና



የሕዝብ ልጅ እንደነበሩ ገልፀው፤ አስከፊው የደርግ ሥርዓት በሕዝቦች መራራ ትግል ከተገረሰሰ በኋላም አገራችን ኢትዮጵያ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት እንድትላቀቅ ከፍተኛ የመሪነት ሚና መጫወታቸውን



ለተሰብሳቢዎቹ በንግግር አሰምተዋል።

ክቡር አምባሳደሩ በዚሁ ንግግራቸው በጠ/ሚኒስትር መለስ ግንባር ቀደም አመራር የተቀየሰው የአምስት ዓመት የእድገትና የትራንስፎሜሽን እቅድ እንዲሳካ፣ ታላላቅ ወይም ሜጋ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁና አገራችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ያለፈው ትውልድ ታጋዮች በከፍተኛ ቆራጥነት ባካሄዱት እልህ አስጨራሽ ትግልና በከፈሉት ከፍተኛ መስዋዕትነት የተገኘውን ድል የአሁኑ

ትውልድ ከእሱ የሚጠበቀውን የእውቀት፣ የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ በማበርከት የተጀመረውን የልማት፣ የዲሞክራሲና የሰላም ትግል የመቀጠል ኃላፊነቱን በብቃት በመወጣት ሰላሟ የተረጋገጠ፣ የበለፀገችና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንዲገነባ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የተሰጠ አደራና የሚጠበቅ ኃላፊነት በመሆኑ ቃላችንን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለብን አስገንዝበዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እለቱን በማስመልከት በጣሊያን ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን መካከል የአገር ሽማግሌዎች፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የአማራ፣ የትግራይና የኦሮሞ ልማት ማኅበራት ተወካዮች የጠ/ሚኒስትሩን ራዕይ መቀበላቸውንና ይህንኑ ከግቡ ለማድረስ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸውን በመግለጽ በየተራ ንግግር ካደረጉ በኋላ የሻማ ማብራት ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖ ተሰብሳቢው ማኅበረሰብ የክቡር አቶ መለስ ራዕይ ለማሳካት ቃል በመግባት የእለቱ ሥነ-ሥርዓት ተጠናቋል፡፡

